ያ ትውልድ

ቀን ፡ ግንቦት ፲፭ ቀን ፪ ሺህ ፮ ዓ.ም. (May 23, 2014)

<u>የከፍተኛ 15 ቀይሽብር ተዋንያን ከፍያለኝ ዓለሙ 22 ዓመት እሥራት ተፈረደበት</u>

ከ«ያ ትውልድ ተቋም» የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

የከበረ ሰላምታችንን በቅድሚያ አያቀረብን፤

May 23, 2014 (ግንቦት ፲፭ ቀን ፪ ሺህ ፮ ዓ.ም.) በሰሜን አሜሪካ ዴንቨር ኮሎራዶ የአረመኔውን ከፍተኛ 15ቱ ቀይ ሽብር ተሳታፊ ከፉለኝ ዓለሙን ጉዳይ የመጨረሻ ፍርድ ውሳኔ ለመስጠት የፍርድ ቤቱ ችሎት ከጠዋቱ 9:30 ተሰየመ። ጉዳዩን ሲከታተሉ የነበሩት ጠበቆችና የሚመለከታቸው ተገኝተዋል። ከፉለኝ ዓለሙን ለመጀመሪያ ጊዜ በዴንቨር ኮሎራዶ በመመልከት ወደ ፍርድ ይቀርብ ዘንድ ከፍተኛውን ድርሻና ኃላፊነት የተወጣው የዴንቨሩ ነዋሪ አቶ ክፍሉ ከተማን ጨምሮ በነሐሴ ፬ ቀን ፪ ሺህ ፭ ዓ.ም. በዴንቨር በተካሄደው የፍርድ ቤት ውሎ በአካል በመገኘት በከፉለኝ ዓለሙ በከፍተኛ 15 እሥር ቤት በ1970/71 ዓ.ም. በጊዜው ወጣቶች፣ ሕፃናትና አዛውንቶች ላይ የፈጸመውን አሰቃቂ ግርፋት፣ ግፍና ግድያ በመመስከር ተገኝተው የነበሩት ወ/ሮ አበበች ደምሴ ከሳንሆዜ፣ አቶ ብርሃን ዳርጌ ከዋሽንግተን ዲሲ፣ ዶ/ር ሳሙኤል ከተማ ከዴንቨር እና አቶ ነሲቡ ስብሐት ከቨርጂንያ ሲገኙ አቶ አሳየኸኝ ፈለቀ ከቦስተን በሥራ ምክንያት አልተገኙም።

በፍርድ ሂደቱ የከፉለኝን ጉዳይ የያዙት ጠበቃ ከፉለኝ ዓለሙ የአሜሪካንን መንግስት በማጭበርበር ባደረገው ማንነትን የማታለል ጉዳይ የ22 ዓመት እስራት እንደሚገባው ፍርድ ቤቱን ጠየቁ። የፍርድ ቤቱ ዳኛ ጉዳዩን ከተለያየ አቅታጫ ካደመጡና ከተመለከቱ በኋላ በዛሬው ዕለት በከፉለኝ ዓለሙ ላይ የ22 ዓመት እስራት ብያኔ ሰጥተዋል።

ነሐሴ ፲፰ ቀን ፪ ሺህ ፬ ዓ.ም. (August 24, 2012) ከፍያለኝ ዓለሙ በሰሜን አሜሪካ ዴንቨር ኮሎራዶ የአሜሪካን ደህንነት ኃይሎች ቁጥጥር ሥር በመዋል ወደ እስር ቤት መግባቱ ይታወቃል። የከፉለኝ ዓለሙን ጉዳይ ሳትሰለቹ በመከታተል እዚህ ላደረሳችሁና የመጨረሻውን ብይን ላሰጣችሁ የከፍተኛ 15 ወገኖችና የያ ትውልድ አባላት ምስጋናችን ይድረሳችሁ። እናመሰግናለን። የያ ትውልድ አባላትና የቀይሽብር ቀጥተኛ ተጠቂ ወገኖችና ቤተሰቦች በመላ እንኳን ደስ አላችሁ።

በአድራጎቱና በአረመኔነቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ይህ ግለሰብ፣ በትዕቢት ያፈሰሰው የንጹሃን ወንድምና እህቶቻችን ደም፤ ዛሬ ከ36 ዓመት በኋላ ተፋራጅና ተሟጋች በማግኘት ከፍያለኝ ዓለሙን ለፍርድ በማቅረብ የመጨረሻውን ብይን እንዲያገኝ ተደርጓል። የያ ትውልድ

ሰማዕታትን ጨምሮ የከፍተኛ 15ቶቹ ብርዬ ሀ/ማርያም፣ ክፍሌ ቄስ፣ ታደሰ ቢፍቱ፣ ግዛው ወረሳ፣ አፈሳ በቀለ፣ በዛ ገ/ሕይወት፣ አሸናፊ በቀለ፣ አሰለፈች፣ ሶፊያ አየለ፣ ዮሐንስ ስዩም፣ ዳንኤል አንጋጋው ወዘተ እና የበርካታ ወጣቶች ደም ምንጊዜም ቢሆን ተፋራጅ እንዳለው እንረዳለን። የበርካታ ወጣቶችንና ጎልማሶችን ደም እንደውሃ አፍስሦ ምንም እንዳልሰሩ አድፍጦ መቀመጥና ይባስ ብሎ ያንን ትውልድ ተጠያቂ ለማድረግ የሚደረገው ሩጫና ታሪክ ብረዛ ተከላካይና ሀቁን አስረጂ ወገን እንዳለው ጥርጣሬ የሚገባን አይመስለንም። ጊዜው ምን ቢርቅ ታሪካችን ተዳፍኖ እንደማይቀመጥና ለትውልድ እንደሚተላለፍ የምናደርገው ጥረት ፍሬ እንደሚያሳይ በያ ትውልድ ስም እያደረግን ያለው እንቅስቃሴ ውጤት መስካሪ መሆኑን «ያ ትውልድ ተቋም» ያምናል።

የከፍተኛ 15ን ቀይ ሽብር ተሳታፊ ከፍያለኝ ዓለሙ ያለበት ቦታ ከታወቀ ጀምሮ ጉዳዩን በመከታተል ሙሉ ትብብርና ድጋፍ ላደረጋችሁ ሁላ ልናመሰግን እንወዳለን። በተለይ ከፍያለኝ ዓለሙ የዛሬ 36 ዓመት የሰራውን ወንጀል የምታውቁትንና ያያችሁትን ለመመስከር ምንም ሳታወላውሉ ፈቃደኛ በመሆን ለተባበራችሁ ዛሬ ከፍያለኝ ዓለሙ ማንነቱ እንዲታወቅ ፍርድ ማለት ምን እንደሆነ ይመለከት ዘንድ ያበረከታችሁት አስተዋጽዖ ውጤት ነውና በሰማህታት ወንድምና እህቶቻችን ስም ከ«ያ ትውልድ ተቋም» ምስጋችን ይድረሳችሁ።

በከፍተኛ 15 ለምትገኙ በደርግ ያንድ ትውልድ መመተር ቀይ ሽብር ጥቃት ሰለባ ለሆናችሁ ቤተሰቦችና ወገኖች በሞላ፡ የዛሬ 36 ዓመት በማንሃህሎኝነት በየእሥር ቤቱና በየመንገዱ የፈሰሰው የልጆቻችሁ ደም ሰሚ ሊያገኝ ችሏል። ጊዜው ምንም ቢርቅ ጉዳዩ ዛሬም ያንገበግባልና ወንጀላቸውን ተሸክመው ማንነታቸውን ደብቀውና አድፍጠው ያሉ መሰል ከፋለኝ ዓለሙ ገዳዮች ምንጊዜም፣ ዛሬም ወደ ሕግ መቅረቡ ለሌሎች ትምህርት ሊሰጥ ይገባዋል እንላለን። ጊዜ የሰጠውን ጉልበትና ኃይል ተጠቅሞ ያለአግባብ የሚፈስ የንጹሐን ደም ሌላ ጊዜ የፍትህ ያለህ ብሎ ወደ ሕግ እንደሚያቀርበው ትምህርት ሊወሰድበት ይገባል። ዛሬ ዓለም የወንጀለኞችና የገዳዮች ዋሻ አለመሆኗን በትንሹም ቢሆን ግንዛቤ እንድንወስድ ይገባል እንላለን።

በ1969/70/71 ዎቹ የደርግ ቀይሽብር ተሳታፊዎች ጉዳይ የሁላችንም የያ ትውልድ አባላትና ቤተሰቦች የጋራ ኃላፊነት ነው ብለን እናምናለን። በመሆኑም በየቦታው አድፍጠው የተቀመጡትን በደም የተነከሩ ወንጀለኞች ቢያንስ በኅብረተሰቡ ሊታወቁ የሚገባቸው በመሆኑ የጉዳዩ ባለቤት ሁላችንም ነንና፤ ድጋፍና ትብብራችን ለግለሰቦችና ለተወሰኑ አካላት ሳይሆን ለሚነሳውና ለተነሳው ጉዳይ መሆኑን በማገናዘብ ድምጻችንን በጋራ እናሰማ እንላለን።

«ያ ትውልድ ተቋም» ከፋለኝ ዓለሙን ለፍርድ ለማቅረብ የሚደረገውን ሂደት ሙሉ ድጋፍ በመስጠት እንደተባበረ ሁሉ በቀጣይነትም በየቦታው አድፍጠው የተቀመጡ የደርግ ቀይ ሽብር ተሳታፊዎችን ከያሉበት በማውጣት ሕዝብ እንዲያውቃቸው ማድረግ ይጠበቅብናልና እንተባበር እንላለን።

እናመሰግናለን

“ያ ትውልድ” ተቋም

Email : yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com, yatewlid@hotmail.com
web site : http://www.yatewlid.com , http://www.yatewlid.org
Facebook: yatewlid